# ለደብተራው (ጸጋዬ ገ/መድኅን)

ከጌትነት



መናገር ቢያቅተኝ ምን አፌ ቢለጎም
በጊዜያዊ ብሽቀት ተስፋዬ ቢጨልም
መኖርህን ነው እንጅ መምትህን አላልም

ድንጋይ ሰብሮ ሩጫ አወይ የጊዜ ቅል
ደብተራውን ገድሎ በዘር መቀማጠል

አወይ የኛ ትውልድ ወይ ዲሞክራሲ
ወያኔ አራት ኪሎ ደብተራው "ፈላሲ"

በሰፈሩት ቁና መሰፈሩ ላይቀር
እድገት ለማት ብሎ ከንቱ መቀባጠር

እነርሱም ይግደሉ እኛም እንሞታልን
የነርሱ ግን ትቢያ እኛ እናብባለን

አቤ ኮሚሳሩ ሥራህ ፈክቶ አብቧል
ስጋህን በሉ እንጅ መንፈስህ መች ሞቷል
ተከታይ ልጆችህ በረድፍ ቆመናል

ምን ምስጥር ቢያደርገው ለአሥርታት ደብቆ
ፈራጁ ይከፍላል በአዲስ ፈራጅ ታንቆ

አንተ ያስተማርከው ሆዱን ካስቀደመ ነጻነቱን ሽጦ
ባርነቱን ይምረጥ ሁሉም ተርመጥምጦ

ኦክቶበር 15. 2014